# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዛደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም።

ቁጥር 23 ቀን 3/7/67

## ስጋ ሰጥተው ቢላያ አይነሱም

የገጠርን መሬት የሕዝብ ለማድረግ ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት የካቲት 25 ቀን ታሪካዊ የሆነውን አዋጅ አውጆአል። በዚሁ እለት 'የሰፊው ሕዝብ ድምጽ' ባወጣው ልዩ እትሙ ላይ ይህንን አዋጅ መደገፉንና ከስራም ላይ ለማዋል ከሚታገሉት ሃይሎች ጋር እንደሚተባበር፣ ከነርሱም ጋር ሆና አድሃሪያችን ለመቋቋም ያለውን ቁርጥ ሃሳብ አስታውቆአል። ሰፊው ሕዝብ ለዚህ ታሪካዊ አዋጅ ያለውን የማያወላውል ድጋፍ በማያወላውል አኳሃን መግለጡን በአዲስ አበባም ሆነ በየክፍለ ሃገሩ የተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች ቋሚ ምስክሮች ናቸው። በዚህ አዋጅ አላማ ተነሳስተው ለብዙ ዘመናት የአድሃሪያችን አመጽ የተቋቋሙት ተማሪያች፣ ተራማጆችና በጠቅላላውም የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ይህ አዋጅ ከስራ ላይ በትክክል እንዲውል ገና ብዙ መስዋእትነትና ትግል እንደሚጠብቃቸው ያውቃሉ፣ ለዚህም ይዘጋጃሉ።

በአሁኑ ጊዜ ይህ አዋጅ በመታወጁ ብቻ የመሳፍንቱ ስርአት አለቀ ደቀቀ፣ በኢትዮጵያ ለዝባዥ መደብ የሚሉ ነገር ጠፋ፣ እያሉ ሕዝቡን ለማዘናጋት የሚሞክሩ እንዳሉ የታወቀ ነው። እነዚህ ክፍሎች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የረቮሉሽኑ እንቅፋት መሆናቸውን መገንዘብ አለባቸው። ትግሉ ገና ነው። ሰፊውን ሕዝብ ትግልህ ተፈፀመ፡እፎይ በል ከማለት ፋንታ የመጭውን ትግል መራራነት እያፍረጠረጡ ቢነግሩት የተሻለ የድል ዋስትና ይኖረዋል።

እንደዚህም ስለሆነ ለመጭው ትግል ለመሰናዳት አንዳንድ ነገሮችን ማጤን ይኖርብናል። የዚህ አዋጅ መሰረታዊ ይዘቶች ምንድን ናቸው? ማንን ይጎዳሉ? ማንንስ ይጠቅማሉ? የረቮሉሽኑ ጠላት ማነው? ወዳጁስ? እነዚህ ጥያቄዎች በጥሞና ተጠንተው መታወቅ አለባቸው። ከታወቁም በኋላ ጠላቶችን መበተን፣ መከፋፈል፣ ማዳከምና መደምሰስ ያስፈልጋል። ወዳጆችን ደግሞ መሰብሰብ፣ ማደራጀትና ወደድል መምራት ያስፈልጋል። ይህ ማንኛውም ከግቡ የደረሰ ረቮሉሽን የተከተለው ትክክለኛ የትግል ዘዴ ነው። ይህንንም ባለመከተላቸውና ወዳጅን ከጠላት በሚገባ ለይተው አስፈላጊያችን እርምጃዎች መውሰድ ተስኖአቸው ብዙ ረቮሉሽኖች በአንጭጭ እንደተቀጩ ታሪክ ደጋግሞ የመዘገበው ነው።

ዝርዝር ከመግባታችን በፊት አንድ አጠቃላይ ነገር ለመጥቀስ እንወዳለን። የዚህ ታሪካዊ አዋጅ መታወጅ የአድሃሪውን ወገን ብቻ ሳይሆን ከመሃል ሰፋሪውም መደብ ብዙዎቹን ወደፀረረቮሉሽኑ ሰፈር ወርውሮአቸዋል። በተለይ ከንኡስ ከበርቴው መደብ አብዛኛው ክፍል ከመጠን በላይ ተደናግጦአል ለጥቅሙ ዋስትና ሊሰጠው የሚችል የተደራጀ ሃይል ስለሌለው መጭው ጊዜ አስጨንቆታል። ተወናብዶም ወደፀረረቮሉሽኑ ሰፈር እየተደባለቀ ነው ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ የረቮሉሽኑ ሃይሎች ሊሰበሰቡ የሚችሉበት ግልጽ የሆነ የትግል አላማ በማግኘታቸው ከመቸውም ይበልጥ ሊጠናከሩ የሚችሉበት ብሩህ የሆነ ሁኔታ አጋጥሞአቸዋል ማለት ነው። ባጭሩ በዚህ አዋጅ ምክንያት የኢትዮጵያ መደቦች በእርግጥ ወገን እየለዩ እየተሰባሰቡ ናቸው። ለወባኙ፡ለሞት ወይም ለሽረት የሚደረገው ታላቅ የመደብ ጦርነት ግልጥ በሆነ ሰንደቅ አላማ ስር በመሰለፍ ላይ ናቸው።

እንግዲህ የረቮሉሽኑን ወዳጆችና ጠላቶች ለማወቅ የዚህን አዋጅ ይዘት ማጤን ያስፈልጋል። በመሰረቱ ይህ አዋጅ ለአፈር ገፊው ጥቅም ሲባል የተደነገገ አዋጅ ነው። ቀጥታና ዋና ተጠቃሚው ለዘመናት እየተበዘበዘ በኑሮ ጠርዝ ላይ ተንጠልጥሎ የቁም ስቃዩን ሲያይ የቆየው አብዛኛው አርሶ በላ ሕዝብ ነው። ሰፊው አርሶበላ ሕዝብ ለኑሮው ይበቃዋል የሚባለውን መሬት በይዞታው ያገኛል። ጥሮ ግሮ ከሚያፈራው ምርት ደግሞ በተቀምጦ በላው ክፍል የሚዛቀው ፍሬ ሊቀርለት ነው። ነገር ግን በዚህ አዋጅ ተጠቃሚው አርሶበላው ብቻ አይደለም። የመሳፍንቱና የሌሎች አድሃሪ ሃይሎች ሃይል

ወርቦ [?] ተሰብሮ ይህ አዋጁ ከስራ ላይ ሲውል ከመሬት የሚገኘው ምርት ይጨምራል::ለከተማው ወዝአደር
የእህል መርከስ:የስራ መስፋፋት:ዋስትና ያለው የደመወዝ እድገት /ከባላገር እየፈለሰ ደመወዝን
ወደታች የሚጫነው የስራአጥ ሰራዊት ስለሚቀንስ/ ይከተላል::በጠቅላላው የገበሬው ኑሮ መሻሻል
ለኢንዱስትሪ:ለንግድ:ለትምህርት:ለጤና:ለመገናኛዎች መስፋፋት ወዘተ. ይህ ነው የማይባል ሰፊ
ሜዳ [?] ይከፍታል::እፍኝ ከማይሞሉት መሳፍንት:መኳንንት:አቀባባይ ከበርቴዎች:ኢምፔሪያሊስቶች:አድ
ሃሪ ከበርቴዎችና ንኡስ ከበርቴዎች ... በስተቀር ይህ ለውጥ በሚያስከትለው እድገት ድርሻውን
የማያገኝ ዜጋ የለም::ስለዚህም ከኢትዮጵያ ሕዝብ 90 በመቶ የሚሆነው ለዚህ ሪቮሉሽን ይሰለፋል::
እንደዚህም እንደሆነ የሬቮሉሽኑ አላማ ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች በፈርጁ በፈርጁ ሲገለጥላቸውና የአ
ድሃሪ አወናባጆች ፀረሬቮሉሽን ፕሮፓጋንዳ በቀጡ መመታት ይገባዋል::

የኢትዮጵያ ሬቮሉሽን ደጋፊዎች እንደዚህ የበዙ ቢሆኑም እፍኝ የማይሞሉ ጠላቶቹ ደግሞ
ያላቸውን ሃይል መናቅ ከጉዳት ላይ ይጥላል::የሕዝቡን ትግል ማዘናጋትና ትጥቅንም ማስፈታት
ይሆናልና::

እነዚህን ጠላቶች በሁለት ገርዶፍ [?] ከፍሎች ልንከፍላቸው እንችላለን::በአንድ በኩል
ሬቮሉሽኑን ለማጥፋት እስከመጨረሻው የማይሰለቹና የማይተኙ አድሃሪ ሃይሎች አሉ::በሌላ በኩል
ደግሞ በመደባዊ ጠባያቸው ወላዋይነት የሚያጠቃቸውና እነርሱንም በሚመለከተው በኩል ተከከለኛ
ዋስትና የማይሰጠው የደርጉ ፖለቲካ አደናግሮአቸው ወደፀረሬቮሉሽኑ ሰፈር ሰመወርወር ላይ ያሉ
ሃይሎች አሉ::እነዚህ ገና ሳይነኩ 'ነገ በኔ' በማለት ብቻ የፈረጠጡ በተለይ የንኡስ ከበርቴው
ወገኖች በአሁኑ የሬቮሉሽን ደረጃ በአጋዥነት ሊሰለፉ ስለሚችሉ በጥንቃቄ ሊያዙና ሊመለሱ ይገባል::

በምንም አይነት ሬቮሉሽኑን ለመደምሰስ የማይመለሱት ሃይሎች —መሳፍንት:መኳንንት:ጳጳሳ
ትና ከፍተኛ የቤተክህነት አለቆችና ርዝራዦቻቸው:ኢምፔሪያሊስቶች:በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ነፍጠ
ኞች:በሰሜንም ሆነ በደቡብ ተወላጅ የሆኑት ከፍተኛ ባላባቶች:አቀባባይ ከበርቴዎች:በቀርቡ የተወ
ረሰው ብሄራዊ ከበርቴና የመደብ ወንድሙ:የንኡስ ከበርቴው የቀኝ ከንፍ:ወዘተ.— በአሁኑ ጊዜ
እነዚህ ሁሉ ሬቮሉሽኑን ለማጥፋት ከምንም የሚመለሱ አይደሉም::በዚህ ሁሉ ላይ እነዚህን አድሃሪ
ሃይሎች ሊያስተባብርና ሊያገዝ የሚችል የቀድሞው ስርአት የመንግስት መኪና ገና በቀጡ አልተነካም::

እነዚህ አድሃሪዎች ለጊዜው የተደናገጡ በመስለም ነፍስ እንደዘራባቸው ተመልሰው ለማንሰ
ራራት መሞከራቸው ባይታለም የተፈታ ነው::ከሰፊው ሕዝብ የተሻለ የድርጅት ልምድ አላቸው፣ በውጭ
ሃገርና በሃገር ውስጥ ያከበቱት ሃብት አላቸው::ተንሰራፍቶ የሚገኘው መሪ ርእዮተአለም/አይዲዮ
ሎጂ/ የነርሱ ነው::ኢምፔሪያሊስቶችም ትግላቸውን ለማገዝና ለማስተባበር ይሞክራሉ::ካሁኑ ኩታ
መገጠም የጀመሩት እነመንገሻ ስዩም:እነነጋ ተገኝ:እነብርሃነመስቀል ደስታ:እነመርእድ ብሩ:እነ
ከበደ ብዙነሽ.... እንደሸረሪት በሃገሪቱ ላይ አድሃሪ ተብብራቸውን ማድራት ጀምረዋል::ከውጭ
አለጋወራሹና የቀድሞው ቢሮክራሲ ርዝራዦች/አምባሳደሮች:ሚኒስትሮች ወዘተ./ በእንግሊዝ:በጀርመንና
በተለይም ደግሞ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች እየተረዱ ፀረሕዝብ አላማቸውን ለማስተባበር በመሞከር
ላይ ናቸው::ገና ብዙዎች ከመንግስቱ ቢሮክራሲና ምናልባትም ከደርጉ ጥምር ወጥተው ከነዚህ ጋር
ይሰለፋሉ::በመጨረሻም የውጭዎቹንና የውስጦቹን አድሃሪዎች ኢምፔሪያሊዝም ያገናኛቸዋል፣ ያስተባብ
ራቸዋል::

ይህንን የአድሃሪዎቹን ሸር ጉድ እንደቀላል ነገር ማየት ወይም ደግሞ አድበስብሶ ለማለፍ
መሞከር የሰጎንዋን ፍልስፍና ይሆናል::ከኛ በፊት የቀደሙትን ሬቮሉሽኖች ታሪክ መመርመርና ከነር
ሱም ትምህርት መቅሰም ያስፈልጋል::የፈረንሳይ ሬቮሉሽን ታሪክ ተሰዶደው የወጡት መሳፍንት ተመል
ሰው የሬቮሉሽኑን እርምጃ ለመግታት እንደቻሉ ያሳያል::የሩሲያ ሬቮሉሽን ታሪክ ከስልጣን የወረ
ዱት አድሃሪዎች በኢምፔሪያሊስቶች እየተረዱ ተመልሰው ሶስት አመት ሙሉ ሰፊውን ሕዝብ አሰቃዩ
የርስበርስ ጦርነት ውስጥ እንደጨመሩት ያሳያል::በቪየትናም የሄድን እንደሆነ ከ1954 የዲየን
ቢየንፉ ድል በኋላ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች በቪየትናም ሕዝብ ላይ የተጫነው የዲየም መንግስት

ረቮሉሽኑ ለአርሶበሌው ያከፋፈለውን መሬት እንደገና ቀምቶ በመውሰድ ሃገሪቱን እስከዛሬ ድረስ ከባድ ጦርነትና ፈተና ላይ እንደጣላት እናያለን:: ቺሌን ያየን እንደሆን በሕዝብ ምርጫ ስልጣን የጨበጠው የአሌንዴ መንግስት ሕዝቡን አስታጥቅ ሲሉት አሻፈረኝ በማለቱ ዛሬ በቺሌ ሕዝብ ላይ የወረደውን የፋሽስት አገዛዝ ፈተና ሁሉም የሚያውቀው ነው:: በኛም አገር ቢሆን ካሁኑ በርግጥ ልናያቸው የምንችላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ:: አንደኛ አድሃሪያቹ በኢምፔሪያሊስቶች የበላይ ጠባቂነት እንደሚሰበሰቡና ብሄርና ሃይማኖት ሳይሉ ፀረሕዝብ አንድነት እንደሚመሰርቱ የታወቀ ነገር ነው:: ሁለተኛ ደግሞ የሞት ወይም የሽረታቸው ትግል መሆኑን ስለሚያውቁት እስከመጨረሻው ድረስ እንደሚፍጨረጨሩ ሳይታለም የተፈታ ነው:: ጠቅላላው ስራዊት ዛሬ ከሕዝቡ ጐን የተሰለፈ ቢሆንም አድሃሪያቸና ኢምፔሪያሊስቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ የራሳቸውን የፀረረቮሉሽን ስራዊት ሊፈጥሩ እንደሚችሉ አይጠረጠርም::

የረቮሉሽናችን ድል ዋስትና የሚያገኘው፣ የዚህ የመራራ ትግል ውጤት የሚሰምረው በአንድ ዘዴ ብቻ ነው:: የሕዝቡ ወገን ከአድሃሪያቹ.ወገን ይበልጥ ስልትና ቆራጥነት ባለው ዘዴ ከነርሱ በልጦ ሲደራጅና ሲታጠቅ ብቻ ነው:: ሌላ ምንም መፍትሄ የለም:: ለዚህ ደግሞ ሰፊው ሕዝብ የገዛ ነፃነት ትግሉን በሚመለከቱት ጊዜያዊና አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ መወያየት: ሃሳቡን መግለጽ: መመካከር ስለሚያስፈልገው ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ያለአንዳች ገደብ ከስራ ላይ መዋል አለባቸው::

መሬት ለአራሹ የሚለውን መሰረታዊ ዲሞክራሲያዊ አዋጅ አውጀ የመናገርን: የመፃፍን: የመሰብሰብን: የመደራጀትንና የመታጠቅን ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች አፍኖ ለያዘ መንግስት 'ስጋ ሰጥተው ቢላያ አይነሱም' እንለዋለን::

ባጭሩ ደግመን ደጋግመን እንዳልነው በርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ወደፊት እንዲራመድ የሚፈልጉ ሃይሎች ተቀዳሚ ተግባራቸው የመደራጀትና የማደራጀት ስራቸውን ማጣደፍ ነው እንላለን:: ጠላቶቻችንም ሃይለኞች ስለሆኑ በዛሬው ወቅት ይህ አዋጅ በስራ ላይ እንዲውል የሚታገሉትን ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ክፍሎች በሙሉ ማደራጀትና ማስተጋገዝ ያስፈልጋል:: እነዚህም ሃይሎች ጪሰኛው: አነስተኛውና ድሃው ገበሬ: ከመሬቱ የተነቀለውና ስራአጥነት ያጠወለገው ባላገር: ወዝአደሩ: አሽከሩ: ገረዲቱ: ሴትኛ አዳሪዋ: ተራማጁ ምሁርና ወታደር: ተራማጁ ተማሪና አስተማሪ: ኢትዮጵያዊው ጭቁን ነጋዴ: በጠቅላላው የንኡስ ከበርቴው ተራማጅ ክንፍና የጭቁን ብሄሮች ተራማጅ ሃይሎች...ናቸው:: የደርጉን ፈቃድ ሳይጠብቁ ተራማጆች ተደራጅተው እነዚህን መደቦችና የሕዝብ ክፍሎች ማደራጀት አለባቸው::

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ በመሰረቱ ዛሬ ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት አላማ ላይ ሊተባበሩ ይችላሉ:: ከዚህ አልፎ በሚመጣው አላማ ግን ሁሉም በአንድነት ሊሰለፉ እንደማይችሉ ግልጽ ነው:: ስለዚህ ዛሬ ከፊታቸው በተደቀነው የጋራ ጠላት ላይ: ሁሉም በሚስማሙበት ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል ላይ ለመተባበር እንዲችሉ ሁሉም በመሰላቸውና በሚያመቻቸው በዲሞክራሲያዊ ዘዴ ተደራጅተው በአንድ የጋራ ረቮሉሽናዊ ግንባር መተሳሰር አለባቸው::

እንደዚህ ከየመደቡ ለተውጣጡና በዘላቂ አላማቸው ለተለያዩ ውስብስብ ሃይሎች ሁሉ ከላይ ሆኜ አንድ 'ተራማጅ ድርጅት' አወረውራለሁ የሚለውን የደርጉን ቢሮክራሲያዊ መፍትሄ ሰፊው ሕዝብ የሚቃወመው እዚህ ላይ ነው:: ነገር ግን እንደዚህ አይነቱ: ማን የት ድረስ እንደሚራመድ ሳይጣራ ሁሉንም በስመተራማጅ አንድ ላይ አምቄና አስተፋፍገ እታገላለሁ የሚል አቋም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል::

ደርጉ: ሰፊው ሕዝብ በመሰለው እንዳይደራጅ ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን አፍኖ ይዞ 'አንድ ተራማጅ ድርጅት' አቋማለሁ ሲል በእውነቱ ምን ለማለት እንደታሰበ ለማወቅ ያስቸግራል:: ነገር ግን በየትም ብንሄድ ይህ ድርጅት የግድ ከሁለት ነገሮች አንዱ መሆን አለበት:: ወይ ሕዝባዊ ረቮሉሽናዊ ግንባር ነው:: ወይም ደግሞ የአንድ የተወሰነ መደብ ፓርቲ ነው::

በሰፊው ሕዝብ ከለል የሚጠቃለሉትን ተራማጅ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም ለመጠበቅ የቆመ ሕዝባዊ ሬቮሉሽናዊ ግንባር ነው እንበል::ግንባር ሲባል መቸም የድርጅቶች ድርጅት ማለት ነው::ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት በሆነው በዚህ ሬቮሉሽናችን በሰራተኛው መደብ ፓርቲ የሚመራ ሕዝባዊ ግንባር እንደሚያስፈልገን ተደጋግሞ የተጠቀሰ ጉዳይ ነው፤ እንመለስበትም:: አንድ ግንባር እንግዲህ ሊጠነክር የሚችለው ከውስጡ ያሉት አባል ፓርቲዎችና ሌሎች የሰፊው ሕዝብ ድርጅቶች ጠንክረው ሲገኙ መሆኑን ለመረዳት ጠንቋይ መቀለብ የሚያስፈልግ አይመስለንም::እንግዲህ ይህ የተራማጆች ድርጅት ግንባር ነው ከተባለን መሪው የሰራተኛው መደብ ፓርቲ የታለ?በውስጡስ የሚሳተፉት የድሉ ዋስትና የሚሆኑን የጠነከሩ ተራማጅ ፓርቲዎችና ሕዝባዊ ድርጅቶች የት አሉ? ብለን እንጠይቃለን::አሁንም ቢሆን ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቹ ተረግጠው የተያዙበት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና እነዚህን የሕዝባዊ ግንባር አውታሮች አለመሰረተም::የመደራጀት መብት ያለ እንዳች ገደብ ታውቆለት ሳይደራጅም ስለግንባር ማውራት ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ይሆናል::

የሰፊው ሕዝብ ሰብአዊ መብቶች ሳይረጋገጡና ዲሞክራሲ ከስራ ላይ ሳይውል ይህ የታሰበው የደርጉ ቢሮክራሲያዊ ድርጅት ፓርቲ ነው ቢባልም ፈጽሞ የሚያዋጣ አይመስለንም::ፓርቲ ሲባል በየትም አገር:በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ለአንድ መደብ ዘላቂ ጥቅም የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚታገል የዚያ መደብ ግንባር ቀደም ድርጅት ነው::ስለሆነም የራሱ መደብ ርእዮተአለም:የራሱ የትግል ስልት:የራሱ የቅርብ ጊዜና የሩቅ ጊዜ አላማ:የራሱ የመደብ ግብ አሉት::እርግጥ አልፎ አልፎ:በተወሰኑ ዘላቂ ግቡን በማያፋልሱ አላማዎች ላይ ከሌሎች መደቦች ፓርቲዎችና ድርጅቶች ጋር አብሮ መሰለፍ ይቻላል::ነገር ግን በምንም አይነት ይህ ትብብር የመደብ ጠባዩንም ሆነ መደባዊ ግቡን አያስተውም::

እንግዲህ ይህ የደርጉ ቢሮክራሲያዊ ድርጅት ፓርቲ ነው ከተባለ የማን መደብ ፓርቲ ነው የሚለው ጥያቄ መመለስ ይኖርበታል::ይህንንም ጥያቄ ለመመለስ 'የወረት ውሻ ስሟ ወለተጴጥሮስ' እንዲሉ በመጠሪያ ስሙ በምንም አይነት ማወናበድ አያስፈልግም::/በነገራችን ላይ:ደርጉ ለፓርቲው የመረጠውን ስም ቢለውጠው ይሻላል? በአለም ታሪክ ውስጥ አስፈሪና አሰቃቂ የሆኑትን ድርጊቶች የሚያስታውስ ስም ነውና::/ ከዚህ አልፎ አንደኛ ይህ ፓርቲ ጠቅላላውን ተራማጅ መደቦችንና ህብረተሰባዊ ክፍሎችን ሊወክል እንደማይችል፤ ሁለተኛ ደግሞ:በርግጥ የየትኛው መደብ ወኪል እንደሆነ ማየትና ማሳየት ያስፈልጋል::

በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉን ተራማጅ መደቦች አቀፍ የሆነ ፓርቲ እናቋቁማለን ማለት ራሱ ፀረሳይንስ የሆነ:የትግሉን ጥራት የሚያደፈርስ:በመደቦች መካከል የተጣራና ወግ የያዘ ትግልን የሚያፍን ፀረሬቮሉሽናዊ አቋም ስለሆነ እውነተኛ ተራማጆች አይደግፉትም::እንደዚህም ስለሆነ አንድ ድርጅት ቁርጥ አድርጎ የአንድ ሬቮሉሽናዊ መደብ ፓርቲ ነኝ ማለትን ትቶ 'ሁሉንም እወክላለሁ' ማለት ሲያጣው ያን ጊዜ ፀረሬቮሉሽናዊ ሚናው ይጀምራል::በታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ የታየው እውነት ይህ ነው::ለመደባዊ ጥቅሜ:በመደባዊ ርእዮተአለሜ ተመርኩዤ ለመደባዊ አላማዬ እታገላለሁ ብሎ በማስታወቅ ግልጥልጥ አድርጎ ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ በታሪክ አምድ ላይ የታየውና በመታየት ላይ ያለው የሰራተኛው መደብ ፓርቲ ብቻ ነው::ሌላው ሁሉ አወናባጅ ነው::ከንኡስ ከበርቴው አንስተን ወደቀኝ እስከከበርቴውና መሳፍንት ስንሄድ በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ሲደራጁና ሲገዙ የመደብ ይዘታቸውን በመሸሸግ የኛ ድርጅት:የኛ ፓርቲ:የኛ መንግስት ለመላው ሕዝብ የቆመ ነው እያሉ መለፈፋቸውና ማወናበድ መቻላቸው ነው::

ስለዚህ ይህ ቢሮክራሲያዊ ድርጅት ፓርቲ ነው ቢባልም የሙሉ ተራማጆች ፓርቲ ነኝ ቢል የሚሸሽገውን የመደብ ይዘት ፈልቆ ማውጣትና ማሳየት ያስፈልጋል::በዚህ መልክ ደግሞ ሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን ገና ሳይጎናፀፍ የወዘአደሩ ፓርቲ ነኝ ቢልም ተቀባይነት አይኖረውም::ለምን?

እርግጥ ነው፣ ደርጉ ሶሻሊዝምን ለመገንባት እታገላለሁ ብሎአል። በዚህ አቋሙ እስካሁን አንዳንድ ቁምነገር ያዘሉ እርምጃዎች ተወስደዋል። ነገር ግን ደርጉ የሚያቋቁመው ድርጅት የሰራተኛ መደብ ፓርቲ ነው ከማለት በፊት ሁለት ነገሮችን ማጤን ያስፈልጋል።

አንደኛ፡ በሃገሪቱ የሚገኙ በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የሚያምኑ ሃይሎች ከአጠቃላይ ቴዎሪ አልፈው በጊዜው የሃገራችን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ የተራ ዴሞክራሲ መብቶች እንኳን ተነፍገው እናያለን። ታዲያ በምን አይነት ዘዴ ነው የሶሻሊዝምን መሰረተሃሳቦች ሙርኩዘው፣ የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ መርምረው ታክቲካቸውን፡ ጊዜያዊ አጣዳፊ ተግባራቸውን፡ ዋና ጠላታቸውን፡ ጊዜያዊ ወዳጆቻቸውን ሳይለዩና ከሰራተኛው ሳይዋሃዱ በምን ፕሮግራም ላይ ነው ይህን ፓርቲ ሊያቋቁሙ የሚችሉት? ነው ወይስ ከላይ ታክቲኩ፡ ስትራተጂው፡ አላማው፡ ይህ ነው፡ በዚህ ስር ተሰለፉ ተብለው ሊታመቁ ነው?

ሁለተኛ ነገር ደግሞ አለ። ይህ የወዛደሩ ፓርቲ በተአምር ተቋቁሞ ብንል በየትኛው አገር ሬቮሉሽን ነው ወዛደሩ ለዴሞክራሲ ሳይታገል፡ በርሱ ፓርቲ ብቻ፡ በርሱ ድርጅት ብቻ፡ በሌሎች ሬቮሉሽናዊ ክፍሎች የተደራጀ ሃይል ሳይታገዝ ሬቮሉሽኑን ከግቡ ያደረሰው! በየት አገር፡ በምንስ ጊዜ ነው የሰራተኛው መደብ ራሱ በመሰለው እንዳይደራጅ ታፍኖ፡ በሶሻሊዝም ስም ተራማጆች እንዳይደራጁ ታግደው ከላይ በተወረወረ ድርጅት ብቻ ድሉን የተጎናፀፈው? አላየንም፣ አልሰማንም።

ባጭሩ ለማለት የምንፈልገው፡ የደርጉ ቢሮክራሲያዊ መፍትሄ የወዛደሩም የሬቮሉሽኑም መፍትሄ አይደለም። እንዲያውም ሬቮሉሽኑን ሊያዳክምና ሊያሰናክል ይችላል። የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ታውቀውላቸው በመሰላቸው መደራጀት አለባቸው። እነዚህም የጋራ የሆነውን ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ትግላቸውን በአንድ በወዛደሩ በሚመራ ሕዝባዊ ግንባር ስር ማስተባበር አለባቸው። በዚህ መልክ የጊዜውን ወዳጆች ሁሉ በመሰብሰብና የጊዜውን ዋና ጠላቶች በመነጠል፡ በተደራጀ ሃይል መምታትና መደምሰስ ያስፈልጋል።

ጥያቄአችንን ደግመን ደጋግመን እናሰማለን። የድሎቻችን ዋስትና ይኸው ብቻ ነውና። ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝ'' የመሰብሰብ ነፃነቱ ይታወቅለት። የጋዜጦች ነፃነት ይታወጅ። የመደራጀት መብቱ ተረግጦ አይያዝ። መሰረታዊና ሰብአዊ መብቶቹ አይታፈኑ። እነዚህን ዴሞክራሲያዊ የሕዝብ መብቶች ረግጦ ይዞ ደርጉ ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ 'ሶሻሊዝም' ይኸውልህ ቢለው መልሱ በጣም አጭር ነው። ጽድቁ ቀርቶብኝ በወጉ በኮነነኝ ይለዋል።

በዛሬው ወቅት ከዚህ ከመደራጀት ጥያቄ ጋር አብሮ የተያያዘ አንገብጋቢ ጥያቄ የሰፊው ሕዝ'' የመታጠቅና ለማይቀረው የርስበርስ ጦርነት ተዘጋጅቶ የመገኘቱ ጉዳይ ነው። ይህ ዛሬ 'መሬት ላራሹ' ከሚለው መሪ ቃል እኩል የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አጣዳፊ ጥያቄ ሆኖአል። የሳምንቱ ሰልፈኛ ጉሮሮው እስኪነቃ የጮኸው ይህንኑ ነው። 'አስታጥቀው መሳሪያውን፡ ገበሬውን!' 'አስታጥቀው መሳሪያውን፡ ወዛደሩን!' ብሎ ከዳር እስከዳር አስተጋብቶአል።

ሰፊው ሕዝብ እንዲህ ስለጠየቀ አንዳንድ አወናባጆች ሰው ሊያጫርሱ ነው እያሉ ማስተጋባት ጀምረዋል። ግን ዛሬ አድሃሪው ወገን ከእግር እስከራሱ የታጠቀና በመታጠቅ ላይ ያለ መሆኑን እናውቃለን። ማስታጠቅ ማለት ሕዝብ ማጨረስ ነው የሚሉት አወናባጆች <u>አለማስታጠቅ</u> ደግሞ ሕዝቡን <u>ማስጨረስ</u> መሆኑን መገንዘብ አለባቸው። ሰፊው ሕዝብ ታጥቆና ተደራጅቶ በሙሉ ንቃት ራሱን መጠበቅና መብቱን ማስከበር ካልቻለ የአድሃርያን መጫወቻ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

በየትም አገር ታሪክ ቢሆን ገዥ መደቦች በገዛ ፈቃዳቸው፡ ሳይዋጉ፡ ከሞቀ ስፍራቸው ወርደው አያውቁም። የርስበርሱ ጦርነት ተወግዶ ለውጡ በሰላም ቢከናወን ሰፊው ሕዝብ የሚጠላ አይደለም። ነገር ግን በዚህ ተአምር ተማምኖ በአሁኑ ጊዜ የመደራጀቱንና የመታጠቁን ተግባር ችላ ሊለው አይችልም። ሰላምን ከፈለግህ ለጦርነት ተዘጋጅ ይላል አስተዋዩ አነጋገር። ስለዚህ አድሃሪያችን ገና በቅጡ ነፍስ ሳይዘራባቸውና ሳይተባበሩ ሰፊው ሕዝብ በተሻለ ተደራጅቶና ታጥቆ ከጠበቃቸው ሰላም ገና ነፃነትን መጎናፀፍ ይቻላል። አለበለዚያ ይህ አዋጅ ከታወጀ በኋላ በልዩ ልዩ ፀረዴሞክራሲያዊ ዘዴዎች ሰፊው ሕዝብ እንዳይደራጅና እንዳይታጠቅ ከታገደ በታሪክ ፊት አስጠያቂ ወንጀል ተፈፀመ ማለት ነው።

እስካሁን ሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቹን ተነፍጎ በመቆየቱ ብዙ ወርቃማ
ጊዜ አለፍአል::አሁንም በየሰአቱና በየደቂቃው አድሃሪያኑ ነፍስ ሲዘራባቸው እየታየ የሰፊው ሕዝብ
መብቶች ጉዳይ እንደቀላል ነገር ተወስዶ ወርቃማው ጊዜ በመባከን ላይ ነው::በመደራጀትና በትጥቅ
ጉዳይ ላይ ሰፊው ሕዝብና አድሃሪያኑ አሽቀድድም ይዘዋል::ስለዚህም ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ባስቸ
ኳይ አለማወጅ አድሃሪያንን የሚያስቀድም/ለአድሃሪያኑ የሚያመች/ አደገኛ አዝማሚያ መሆኑ መታወቅ
አለበት::

የሆነ ሆኖ በዚህ አጣዳፊና ታሪካዊ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሰፊ.ሕዝብ እንደህይወት እስትንፋሱ
የሚያስፈልገው የዲሞክራሲ መብቶችና የመደራጀት ጉዳይ እንደቀላል ነገር የሚታይ አይደለም::አዱሉ
ንም በገዱ በደርጉ ውስጥ በደርጉ ውስጥ ተራማጅና አድሃሪው ወገን ከሚያደርጉት ትግል ጋር ማያ
ያዝ የለበትም::እርግጥ በደርጉ ውስጥ የሰፊው ሕዝብና የተራማጅ ወታደር ወገን ነን የሚሉት ሃይ
ሎች ቢያይሉና እነዚህ ሕዝባዊ መብቶች ቶሎ ቢታወጁ የሰፊው ሕዝብ ትግል በጣም ሊፋጠንና ሊገስ
ገስ ይቸላል::ነገር ግን ይህ የሞት ወይም የሽረት ትግል ነውና የኢትዮጵያ ተራማጆች የተቸገሩትን
ተቸገረው ራሳቸውን ማደራጀትና ይገባቸዋል::ይህን ተግባር ከመቸውም ይበልጥ ሊገፉበት ይገባል::
ለዚህ ለታጠቀበት አላማ ከዚህም በፊት የማንንም ፈቃዱ ጠይቀው አያውቁምና አሁንም 'ፈቃዱ እስኪ
ሰጣቸው' ቁጭ ብለው መጠበቅ የለባቸውም::አይጠብቁምም::

ከእንግዲህ እንደሆነ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደነፃነቱ የሚያደርገውን ጉዞ ከፀሃይ
በታች ሊቋቋመው የሚችል ምንም አይነት ሃይል የለም::እስከዛሬ በሕዝቡ ጉን ተሰልፈው ለመማርና
ለማስተማር፣ ለማደራጀትና ለትግሉ አቀጣጪ ለመስጠት በታላቅ መስዋእትነት ሲታገሉ የቆዩት ተራማጆች
ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ለአንድነታቸው መጣር ይኖርባቸዋል::ይህ የመሬት አዋጅ ሰፊውን ሕ
ለማደራጀት ይህ ነው የማይባል አዲስና ታሪካዊ አጋጣሚ ከፍቶላቸዋል::በዚህም አጋጣሚ ታሪክ በት
ከሻቸው ላይ የሚጥለውን አደራ አንድነታቸውን አጠንክረው ሊቀበሉት ይገባል::ስለዚህ በአሁኑ ወቅት
የሰራዊቱ ተራማጅ ክንፍና በጠቅላላው የኢትዮጵያ ተራማጆች አንድነታቸውን ከብረት አጠንክረው:ለሰ
ፊው ሕዝብ እንደህይወት እስትንፋስ የሚያስፈልጉት ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ በግንባር
ቀደምነት መታገል አለባቸው::

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ!
እንደራጅ! እናደራጅ!
ለማይቀረው የርስበርስ ጦርነት እንዘጋጅ!